# ዓይን ይጠበቅ!

'ሀ ሁ!' እያልን ስንማር
ፊደሉን ስንቆጥር
ከሚካኤል ደብር
ከየኔታ እግር
ትምህርት ቤት ገብተን
መሬት ተቀምጠን
ኣቡጊዳ ስንል
መልእክተና ወንጌል
ራሳችንን ቁልቁል
ኣዘቅዝቀን ደፍተን
ዳዊት እየደገምን
ሴቱም ባንድ ወገን
ከየኔታ ቀኝ ጐን
'ሀ ሁ!' ሲያነበንቡ
ሻሹን ሲከናነቡ
ኣንዱ ቀን ያሳተው
ኣላስችልህ ያለው
ቀና ብሎ ቅጽበት
ቆንጂትን የሚያያት
ኣያልፍ ያችን ዕለት
ወዮለት፣ ወዮለት!

የኔታ ጨካኝ ናቸው
ተማሪም ኣይወዳቸው
ከግራው እጃቸው
ይታያል ጭራቸው
ከቀኙም በጐናቸው
የሚታይ ኮርማዠቸው
ማነው የሚደፍራቸው
ቀና ብሎ 'ሚያያቸው?

ምን ጊዜም ያልታደለ
ያ ግርማሁን ታከለ
ፈጽመው ኣይወዱት
ወትሮ ሲያዋክቡት
በጣም ነው 'ሚጠሉት
"ይህ መናጢ፣ ሰነፍ
ሁሌም ሲክለፈለፍ
ቅንዝር ዓይኑ ኣያርፍ
ቆንጂትን ሲመኛት
እጅ፣ ከፍንጅ ያዝኩት!"
ኣሉና በንዴት
በኩርኩም ነረቱት
በመዳፋቸው ሰፊ
ጆሮ ግንዱን በጥፊ
ዘርግተው ረዥሙን
ሰንዝረው ኮርማዡን
ቁንጥጫም ኣከሉበት
መዓት ኣወረዱበት
በኩርኩም ደጋግመው
ናላውን ኣዙረው
ጣሉት ያለ ምሕረት
ኣፈር ደባለቁት…

ግርማሁን ያን ሰዓት
ወደቀና መሬት…
ሽንቱንም ለቀቀው
ዙሪያ ኣጥለቀለቀው
ዓረፋ እየደፈቀ
ጮኸ ተንፈቀፈቀ

ታድያ እማሆይ ሙሉ
ፈጥነው ሊገላግሉ
ገቡና እየዘለሉ፤
"የኔታ ምነው! ምነው!
የሰው ልጅ ሊገድሉ ነው
በቃዎት ይተዉ እንጅ፣
እንዳይሞት ይሽ ልጅ…"
ኣስጣሉት ቶሎ ብለው
ግምባሩን ኣሻሽተው
ግርማሁንን ኣንስተው
ትንሽ ነብስ እንደዘራ

“እማይ!” ብሎ ተጣራ
“አይዞህ ልጄ!” እያሉ
ስመው እያባበሉ
ራሱንም ደባበሰው
ለቅሶው አረሳስተው
ከረሜላ መሳይ
ማንም ሰውም ሳያይ
ደብቀው ሰጡትና
ወደኛ አምጥተው
ቦታው አስቀምጠው
ሲበርድ ያ ሁሉ ቁጣ
ፈገግ እያለ መጣ።

ነገሩ አለፈና
ዱላውም ተረሳና
ማታ ሲበታተኑ
በፀሎት ሲለምኑ፤
“የኔታ ይኑሩልን ለዘላለም
ትምህርቱን ግለጽልን መዳንያለም
በየኔታ ጉረሮ
የጥዋት ቅቤ ነጥሮ
ማታም ጠጅ ከቆርቆሮ
ብርሌ ተንቈርቁሮ…
ግን በእኛ ጉረሮ
አጥንቱ ተቀርቅሮ
በሽምብራ በአሻሮ
ሌሊቱ ነግቶ አድሮ
ጥዋት ጓሮ፣ ለጓሮ…”
እያልን ተበታተን።

ተንኰለኛው ታከለ
በቀልድ እያስመሰለ
ከሁሉም ፈንተት ብሎ፣
ቆንጂትን ተከትሎ
ትንሽ ወጣ እንዳሉ
ከጉብታው መሃሉ
አረ ሰዎች ጉድ በሉ!
ለካስ ይሳሳማሉ…

ከረሜላው ሰጥቷት
በዚያም አግባብቷት
አንቆ ነው የሳማት!

የኔታ ይህን ቢያውቁ
ራሳቸውን ባነቁ!
ላይን ማየት ሲጨነቁ
መሳሳም ቢያዩ ኖሮ
አገር ጠፉ ዘንድሮ!

ታድያ ልጆች ሳለን
የኔታ የሚሉን
ሁሉን የሚመክሩን
ፊደል ያስቀጠሩን
አንድ ብለን እየያዝን
መልእክተን ያስጠኑን
ዳዊት ያስደገሙን
በተለይ ያስማሉን
“ዓይን ይጠበቅ!” ያሉን
አንረሳም ያንን…

ግን ግርማን የመሰለ
የሰይጣን ቁራጭ አለ
ደክመው አቶ ታከለ
የኔታ እንዲቀጡት
ለዚህ ነበር ያመጡት፣
የኔታም እንደዓቅማቸው
ግዴታ ሆኖባቸው
ስንቴ ቢቀጠቅጡት
ጠባዩን አይለውጡት
ቢያለሙት የማይለማ
ቢመክሩት የማይሰማ
ተሟሽቶ አይሟሽ
ወይም አይኮላሽ፤
“ይኸ የዲያብሎስ ሽንት
ይውረድበት መዓት!”
ብለው ረግመው ተውት።

ገ/እ. ጐርፉ።